**ማስጠንቀቅያ/ የክረምት ኣውሎ ነፋስና ማእበል**

**እውነታዎች:** በኣሁኑ ግዜ የሲያትል ኣካባቢ እጅግ ብርቱ በሆነ የክረምት ኣየር እየተሰቃየ ነው። የበረዶ መከማቸትና ቀዝቃዛ ኣየር መደበኛ የመጓጓዣ ኣገልግሎቶችን የሚያስተጓጉሉ፡ የእርዳታ ሰጪ መኪናዎች ከቦታ ቦታ በደንብ እንዳይንቀሳቀሱ እክል የሚፈጥሩና ኣስጊ የሆነ የጤና ሁኔታ ላላቸው ሰዎች የበለጠ እንቅፋት የሚፈጥሩ ናቸው። የተራዘመ የብርድ ሁኔታ ሲኖር፡ የውሃ ቧምቧዎች ወደ በረዶ እንዲቀየሩና እንዲሰበሩም ስለሚያደርግ በመኖርያ ቤቶች የውሃ ችግር ያስከትላል።

**ምን መደረግ ኣለበት:**

- ሙቀት ለማግኘት ብዙ ልብሶችን መደራረብና ልብሶች እርጥበት እንዳይዙ ማድረግ። ከራስ ሰውነት/ገላ የሚገኝ ሙቀት እንዳይጠፋ፡ቆብ/ባርኔጣ ማድረግ።
- ሰው በሚራመድባቸውና መኪና በሚሄድባቸው በቤቶች ኣካባቢ የጣለውን በረዶ ለማቅለጥ በረዶ ማቅለጫ መሳርያ ተጠቀሙ።
- በቤትዎ ውስጥ ኣስፈላጊ የምግብ ዓይነቶችንና ጠቃሚ ነገሮችን ማከመቸት። ኣደጋ ሲያጋጥም ባለሱቆች ሱቃቸውን ለመሙላት ብዙ ግዜ ሊፈጅባቸው ይችላልና።
- በረዶ በሚጠርጉበት ግዜ ከመጠን በላይ ከመድከም ይጠንቀቁ። የሚቻል ከሆነም፡ በሮዶውን ከመሸከም ይልቅ፡ በረዶውን ለመግፋት ሞክሩ።
- በህዝባዊ ማመላለሻዎች ላይ ኣንዳንድ ለውጦችና መዘግየት ሊኖር እንደሚችል መረዳት።
- መብራትም ሊጠፋ እንደሚችል ማውቅና ሌላ ኣማራጭ የመብራት ዘዴዎችን ሲጠቀሙ፡ ጥንቃቄ ማድረግ ኣስፈላጊ ነው።
- ኣደጋውን በሚመለከት ኣዲስ መረጃ እንዳለ ለማወቅ በቀጣይነት ሬድዮ ተከታተሉ።
- ***ይህንን መልእክት ለመረዳት፡ ለማየትም ሆነ ለመስማት የማይችል የሚያውቁት ሰው ካለ፡ እባክዎትን መልእክትቱ ኣስረዷቸው።***

**ጠቃሚ ዌብሳይቶች:**

http://www.seattle.gov/emergency-management/what-if/hazards/snow-ice-and-extreme-cold

http://www.seattle.gov/light/sysstat/

http://www.ready.gov/winter-weather

http://www.redcross.org/prepare/disaster/winter-storm